# የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦት

ከዚህም ባሻገር በአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች በመታገዝ በርካታ የጀነቲክ ሀብቶችንና የማህበረሰብ እውቀቶችን መጠነኛ ለውጦች በማድረግ የአእምሯዊ ንብረት ብቸኛ የባለቤትነት መብት ተወስዶባቸዋል።

ስለዚህ በጣም ተፈላጊ የሆነውን የጀነቲክ ሀብት በምርምርና ትምህርት ስም ወይም በአነስተኛ ጥቅማጥቅም በመደለል ወይም በህገወጥ መንገድ ወስደው ሲጠቀሙ ቆይተዋል። ከዚህ የተነሳ ብዝሀ ሕይወትን ለመጠበቅ፣ በአግባቡ ለመጠቀምና ጥቅሙን በፍትሃዊነት ለመካፈል ሲባል በብዝሀ ሕይወት ባለጸጋ የሆኑ ሀገሮች አነሳሽነት እ.ኤ.አ በ1992 ዓ.ም የብዝሀ ሕይወት ስምምነት ሰነድ ተዘጋጅቶ በርካታ ሀገራት ፈርመዋል። ኢትዮጵያም የብዝሀ ሕይወት ስምምነት ከፈረሙት ሀገሮች አንዷ ናት። ይህ ሰነድ አንድ ሀገር በብዝሀ ሕይወት ሀብቱ ላይ ሉዓላዊ ባለቤትነት መብት እንዳለውና የብዝሀ ሕይወት ሀብቱን ለሕዝቦች ጥቅምና ብልጽግና ሲባል በአግባቡ መጠበቅና በዘላቂነት ጥቅም ላይ ማዋል ያለበት መሆኑን ይደነግጋል። በተጨማሪም የብዝሀ ሕይወት አካል የሆነውን የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰቦች እውቀት ዝውውርና አጠቃቀም አግባብ ባለው ሕግ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ይመክራል።

## የባለድርሻ አካላት ሚና

የብዝሀ ሕይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት በአዋጅ በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት መሠረት የኢትዮጵያ ጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰቦች ዕውቀት በአግባቡ እንዲጠበቅና በዘላቂነት ጥቅም ላይ እንዲውል፣ ከሀብቱ አርክቦት ፍትሀዊ ጥቅም እንዲገኝ የሚያስችሉ አስፈላጊ አዋጆችን፣ ህጎችንና ደንቦችን እንዲወጡ በማድረግ ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል። ስለሆነም የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦትና የማህበረሰብ መብቶችን አዋጅ ቁጥር 482/1998 እና ደንብ ቁጥር 169/2001 መሠረት በማድረግ የተጣለበትን ኃላፊነት በመወጣት ላይ ይገኛል።

በዚህ መሠረት መላው የኢትዮጵያ ሕዝቦችና ማህበረሰቦች፣ የመንግስትና የግል ድርጅቶች፣ ማንም ሰው ወይም ድርጅት በአዋጁ ተለይቶ ካልተፈቀደ በስተቀር የጀነቲክ ሀብትን ወይም የማህበረሰብ ዕውቀትን ለመሰብሰብ፣ ለመውሰድ፣ ለማስተላለፍ ወይም ለመጠቀም ከብዝሀ ሕይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት ፈቃድ የተሰጠ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው።

በተለይም የአካባቢ ማህበረሰቦችና የመስተዳድር አካላት ማናቸውም ሰው ፈቃድ ሳይኖረው የጀነቲክ ሀብት ከአካባቢው እንዳይሰበስብና እንዳይወስድ የመከልከል፣ ፈቃድ ያለው መሆኑን የማረጋገጥና ለሚመለከተው አካል የማሳወቅ ኃላፊነት አለባቸው። የጉምሩክ ባለሥልጣኖች ከሀገሪቱ የሚወጣ የጀነቲክ ሀብት የመውጫ ፈቃድ ከብዝሀ ሕይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት የተሰጠበት መሆኑን የመቆጣጠር፤ ከሀገር የማስወጫ ፈቃድ የመጠየቅና አስፈላጊው ፈቃድ ሳይኖር ከሀገር በመውጣት ላይ የሚገኝ የጀነቲክ ሀብትና በማስወጣት ላይ የሚገኝ ሰው ወዲያውኑ በአካባቢው ለሚገኝ አግባብነት ላለው የፍትህ አካልና ለኢንስቲትዩቱ ማሳወቅ አለባቸው። የፖስታና ሌሎች የፈጣን መልዕክት አስተላላፊ ድርጅቶች ደንበኞቻቸው የጀነቲክ ሀብትን ከሀገር ለማስወጣት ከብዝሀ ሕይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት የተሰጣቸውን ፈቃድ እንዲያቀርቡ መጠየቅ ይጠበቅባቸዋል። የኳራንቲን ተቆጣጣሪ መ/ቤቶች ለህይወታዊ ሀብት ምርት የሚሰጡት የኳራንቲን ሰርተፍኬት በሕይወታዊ ሀብቱ ውስጥ የሚገኝን የጀነቲክ ሀብት ለመጠቀም የሚያስችል ፈቃድ አለመሆኑንና በኳራንቲን ሰርተፊኬቱ በሕይወታዊ ሀብቱ ውስጥ የሚገኝን የጀነቲክ ሀብት መጠቀም የተከለከለና ወንጀል መሆኑን የሚገልጽ መልዕክት እንዲይዝ ማድረግ አለባቸው።

ባጠቃላይ ህጉንና ተመሳሳይ ስምምነቶችን ተግባራዊ በማድረግ ከጀነቲክ ሀብትና ከማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦት በሚገኘው ጥቅም ጀነቲክ ሀብትን በዘላቂነት ለመጠበቅ ብሎም ለሕዝቦቹ ጥቅምና ብልጽግና እንዲውል ሁሉም ባለድርሻ አካላት በጋራ መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል።

**የብዝሀ ሕይወት ሀብቶቻችን የዕድገት መሠረት ናቸው!**

መስከረም 2003 ዓ.ም









### ተጨማሪ መረጃ

የጀነቲክ ሀብት ዝውውር ፈቃድና ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት

ብዝሀ ሕይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት

ፖ.ሣ.ቁ 30726 ሥ.ቁ. 0116612244/0116512028

ፋክስ 0116613722 ድረገጽ፤ www.ibc-et.org

ኢሜይል info@ibc-et.org

አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ

## መግቢያ

የጀነቲክ ሀብት ማለት ለሰው ልጅ ጠቀሜታ ያለው ወይም ወደፊት ጠቀሜታ ሊኖረው የሚችል የሕይወታዊ ሀብትን (እጽዋት፣ እንስሳትና ደቂቅ አካላት) የዘር ባህሪ የያዘ የጀነቲክ ቁስ ሲሆን ከነዚህ የሚገኘውን ተዋጽኦን፤ ማለትም ዘይቶችን፣ እጣኖችን፣ ሙጫዎችን፣ ኘሮቲን፣ በማዳቀል የተገኙ ዝርያዎችን፣ ዓይነቴዎችን እና የመሳሰሉትን ይጨምራል:: እነዚህ የጀነቲክ ሀብቶች የብዙ ሺህ ዓመታት የዝግመተ ለውጥ ሂደት ውጤቶች ናቸው:: በሌላ በኩል ከጀነቲክ ሀብቶች ጋር ተያያዥ የሆነው የማህበረሰቦች ዕውቀት የጀነቲክ ሀብት ማንበርን ወይም መጠቀምን በሚመለከት የአካባቢ ማህበረሰቦች የፈጠሩት ወይም ለዘመናት ያዳበሩት ዕውቀት፣ አሰራር፣ ፈጠራ ወይም ጥበብ ነው:: ኢትዮጵያ ሰፊ የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰቦች ዕውቀት ተለያይነትና ስብጥር ባለቤት ነች:: በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ የእጽዋት እና የእንስሳት ዝርያዎች በርካታ ናቸው:: በኢትዮጵያ ለሚገኘው ሰፊ የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት ተለያይነትና ስብጥር ዋነኞቹ ምክንያቶች፤ 1) የሀገሪቱ የመልካ ምድር አቀማመጥ እና የአየር ንብረት ሁኔታ ተለያያነት፣ 2) የህዝቦች የባሕል ተለያይነት፣ 3) በአብዛኛው በግብርናና በተፈጥሮ ሀብት ላይ የተመሠረተ የኑሮ ሁኔታና የመሳሰሉት ናቸው:: ይሁን እንጂ እነዚህ ጀነቲክ ሀብቶች በሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት ለከፋ ጉዳትና ጥፋት ተዳርገዋል:: እነዚህንም ሀብቶች ጠብቆና በአግባቡ ተጠቅሞ በተገቢው መልኩ ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፍ ካልተቻለ ከጠፉ በኋላ መልሶ ለማግኘት ወይም ለመተካት አዳጋች ይሆናል:: በዚህ የማስገንዘቢያ ጽሁፍ የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ እውቀት ጠቀሜታ፣ አርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት ምንነትና የቁጥጥር አስፈላጊነት እንዲሁም የባለድርሻ አካላት ሚና በአጭሩ ቀርቧል::

### የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት ጠቀሜታ

የጀነቲክ ሀብቶችን መጠቀም ማለት ጠቃሚ ባህሪ ያቸውን በመለየት ሣይንሳዊ እውቀትንና ግንዛቤን ለማሳደግ ወይም ለንግድና ለሌሎች ግልጋሎቶች የሚውሉ ውጤቶችን ማግኘት ማለት ነው:: ላለፉት አሥርት ዓመታት የታየው የጥበበ ሕይወት እድገትና ልቀት ጀነቲክ ሀብቶችን ለመሰረታዊ አገልግሎቶች ከማዋል ባሻገር አዳዲስ ውጤቶችን ለማግኘት አስችሏል:: የጀነቲክ ሀብቶች ለንግድ እና ንግድ ላልሆኑ አገልግሎቶች ይውላሉ::

የንግድ ግልጋሎት የጀነቲክ ሀብቶችን በግብዓትነት ተጠቅሞ የተለያዩ ለንግድ የሚውሉ ውጤቶችን ማለትም የተለያዩ ኢንዛይሞች፣ ልውጠ ሕያዋን፣ ጥቃቅን ሞለኪዩሎችንና የመሳሰሉትን ማምረት ያጠቃልላል:: እነዚህ ውጤቶች የግብርና ምርቶችን ምርታማነት ለማሻሻል፣ ከበሽታና ከተባይ ለመከላከል፣ መድሃኒቶችን ለመቀመም፣ እንዲሁም የኢንዱስትሪ ውጤቶችን ለማሻሻል በግብዓትነት ይውላሉ:: ለንግድ ያልሆኑ ግልጋሎቶች ሲባል የጀነቲክ ሀብቶችን ለትምህርት፣ መዝናኛ፣ ባህላዊ እንቅስቃሴዎች እንዲሁም ለጥናትና ምርምር ማዋልን ያጠቃልላል:: ይህ ግልጋሎት ብዙውን ጊዜ በማህበረሰቦች፣ በትምህርትና በምርምር ተቋማት አካባቢ የሚከናወኑ ተግባራትን ይመለከታል:: ይሁን እንጂ ለንግድ በሚውሉና ለንግድ በማይውሉ ግልጋሎቶች መካከል ግልፅ የሆነ ድንበር የለም:: አንዳንድ የንግድ ተቋማት ከትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር አዳዲስ ለንግድ የሚውሉ ግኝቶችን ለማውጣት ምርምር ሊያደርጉ ይችላሉ:: በሌላ በኩል ለንግድ ዓላማ ያልታሰቡ የምርምር ውጤቶች ለንግድ ሊውሉ ይችላሉ::

በተመሳሳይ ሁኔታ የሀገራችን ማህበረሰቦች የጀነቲክ ሀብቶችን ለዘመናት ለምግብነት፣ መጠለያ፣ መድሃኒትና መዋቢያነት ከማዋል አልፈው ልዩ ባህሪዎችን በመምረጥ ለተለያዩ አገልግሎቶች አውለዋቸዋል:: ይህ ዕውቀት ለዘመናዊ ሣይንስና ቴክኖሎጂ መሰረትና አቋራጭ መንገድ መሆኑ እርግጥ ነው:: ለምሳሌ ድርቅን የሚቋቋሙ አዳዲስ የሰብል ዝርያዎችን ለማግኘት ማህበረሰቦች በደረቃማ አካባቢዎች ያላመዷቸውን ዝርያዎችና ተያያዥ ዕውቀታቸውን ማጥናት ለምርምር የሚውለውን ጊዜ፣ ጉልበትና ገንዘብ ወጪ ይቀንሳል:: በቀላል ምሳሌ ብናየው በገንቢ ንጥረ ነገር የበለፀገ የማሽላ ዝርያን/ዓይነቴን ለመምረጥ ማህበረሰቦች ለዘመናት ያካበቱትን ዕውቀት መሰረት በማድረግ ስያሜዎችን (ለምሳሌ፣ ወተት በጉንጩ) መመርመር ለውጤታማ ግኝት ይረዳል:: ከዚህ ጋር በተያያዘ በርካታ ተጨባጭ ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል፤ ጤፍ (ግሉትኒን ነፃ)፣ ገብስ (ቫይረስን የሚቋቋም)፣ ቡና (አነስተኛ ካፌን)፣ ኮሶ ዛፍ (ጸረ-ኮሶ ትል መድሃኒት)፣ ላክቶ ባሲለስ የተባለ ደቂቅ አካል (እርጎና ዓይብ ለማምረት)፣ ወዘተ በተለያዩ የውጭ ሀገራት ኩባንያዎች ከሀገራችን ተወስደው ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች እየዋሉ ናቸው::

### የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦት

ከጀነቲክ ሀብትና ቴክኖሎጂ ዕድገት አንፃር ዓለም በሁለት ጎራ ልትከፈል ትችላለች:: በአንደኛው ወገን ከፍተኛ ብዝሀ ሕይወት ጸጋ ያላቸውና በቴክኖሎጂ ያላደጉ፤ በሌላኛው ጎራ በቴክኖሎጂ ከፍተኛ ደረጃ የደረሱ ነገር ግን በጀነቲክ ሀብት ባለፀጋ ያልሆኑ ይገኛሉ:: በቴክኖሎጂ ከፍተኛ ደረጃ የደረሱ ሀገሮች ለግብርናና ጥበበ ሕይወት ነክ ለሆኑ ሥራዎች የኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃዎች የሚያገኙት የጀነቲክ ሀብት ባለፀጋ ከሆኑ ሀገሮች ነው:: በሌላ በኩል ለትምህርት፣ ለምርምርና ብዝሀ ሕይወትን ለማበልፀግ የጀነቲክ ሀብቶችን በተለያዩ አካላት ሊዘዋወሩ ይችላሉ:: ይህ ሂደት አርክቦት በመባል የሚታወቅ ሲሆን፤ የጀነቲክ ሀብትን ወይም የማህበረሰብ ዕውቀትን መውሰድ፣ ማዘዋወር፣ ማስተላለፍ፣ ወይም መጠቀምን ያጠቃልላል:: አርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት ከሦስቱ የብዝሀ ሕይወት ዓለም አቀፍ ስምምነት ዓላማዎች ውስጥ አንዱ ነው:: የአርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት ህግ መኖር ለጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰቦች እውቀት ሰጪና ተቀባይ አካላት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው:: ማለትም በሁለቱ አካላት መካከል ፍትሃዊ የጥቅም መጋራት እንዲሰፍን ያደርጋል፤ የቴክኖሎጂ ሽግግር እና የምርምር ልምድ እንዲዳብር ይረዳል፤ በዚህም መሠረት የጀነቲክ ሀብቱ ጥበቃና ልማት እንዲጠናከር ያግዛል::

ስለዚህ የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰቦች ዕውቀት አርክቦት በማህበረሰቦች መልካም ፈቃድና የጥቅም ተጋሪነት ላይ የተመሰረተ ሆኖ በጥቅም ላይ እንዲውል ያስፈልጋል::

### የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦት ቁጥጥር አስፈላጊነት

እ.ኤ.አ ሰኔ 1992 ዓ.ም የብዝሀ ሕይወት ዓለም አቀፍ ስምምነት ከመደረጉ በፊት አንድ ሀገር የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ እውቀት ሉዓላዊ የባለቤትነት መብት አልነበረውም:: የጀነቲክ ሀብትም ሆነ የማህበረሰብ እውቀት የሰው ልጅ የጋራ ሀብት ተደርጎ ይወሰድ ስለነበር ሀብቱ ያለምንም ጥያቄ ማንም ከአገር አገር በማዘዋወር መጠቀም የሚችልበት ሁኔታ ነበር:: በመሆኑም በምጣኔ ሀብት የበለፀጉ አገሮች በብዝሀ ሕይወት ከበለፀጉ ደሀ አገሮች በርካታ የጀነቲክ ሀብቶችንና የማህበረሰብ እውቀቶችን በመውሰድ ለተለያዩ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች በመጠቀም ከፍተኛ ትርፍ ሲመዘብሩበት ኖረዋል::





